# አልኢስቲአዛ ወልበስመላህ

## አለኢስቲአዛ

የተጅዊድ ምሁራኖች ማንኛውም ሰው ቁረን ለማንበብ በሚፈልግበት ጊዜ አኡዙ ቢላሂ ብሎ መጀመሩ አስፈላጊ ነው ይላሉ። ምክንያቱም አላህ ሱብሃነሁ ወተአላ በሱረቱ አንነህል ላይ እንዲህ ስለሚል ነው።

<<ቁርአንን ባነበብህ ጊዜ ርጉም ከሆነው ሰይጣን በአላህ ስም ተጠበቅ፣>>ሱረቱ ነህል

## ኢስቲአዛ የምትደበቅበትና ግልፅ የምጦንበት ቦታ

ኢስቲአዛን በአራት ቦታዎች ላይ በድብቅ ማንበብ ይወደዳል።

1. የሚያነበው ሰው በድብቅ(ድምፁን ዝቅ አድርጎ በሚያነብበት)ጊዜ
2. የሚያነበው ሰው እየጮኸኸና ብቻውን በሚሆንበት ጊዜ
3. ሶላት ውስጥ ሆኖ በሚያነብበት ጊዜ
4. የሚያነበው ሰው በሀለቃ መካከል ከሆነና ሀለቀተል ቁርአኑን ጀማሪ ካልሆነ ኢስቲአዛን ድምፅን ዝቅ አድርጎ ማንበብ ይወደዳል።

## ኢስቲአዛ ግልፅ መሆኑ የሚወደድበት ቦታ

ኢስቲአዛ በሶስት ቦታዎች ላይ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ ይወደዳል።

1. አንባቢው እየጮኸ የሚያነብ ከሆነና ቂረቱን የሚያዳምጥ ሰው ካለ
2. በዝግጅት መክፈቻ ጊዜ
3. በሀለቀተል ቁርአን መካከል ሀለቀተል ቁርአኑን ጀማሪ ከሆነ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ ይወደዳል።

## አልበስመላህ

በማንኛውም ቁርአንን ከመጀመሪያ ሱራ ጀምሮ በሚያነብ ሰው ላይ ከሱረቱ ተውባ በስተቀር በሁሉም ሱራ መጀመሪያ ላይ <<ቢስሚላሂ ረህማኒ ረሂም>> ብሎ መጀመሩ ግዴታ መሆኑን ሁሉም የተጅዊድ ምሁራኖች ይስማማሉ።

ማንኛውም ቁርአን አንባቢ ቁርአንን ከመጀመሪያ ሱራ ጀምሮ የሚያነብ ከሆነ ኢስቲአዛንና በስመላን በማሰባሰብ በአራት አይነት ሁኔታዎች ማንበብ ይችላል።

1. ሁሉንም መቁረጥ

2. ሁሉንም ማያያዝ
3. ኢስቲአዛንና በስመላን በማያያዝ ሱራውን መቁረጥ
4. ኢስቲአዛን በመቁረጥ በስመላውንና ሱራውን ማያያዝ

ነገር ግን ሱረቱ ተውባን የመጀመቲያ ሱራ አድርጎ በሚያነብበት ጊዜ በሁለት አይነት መንገዶች ማንበብ ይችላል።

1. አኡዙቢላሂ በማለት ማቆም ከዚያም በረአቱ ብሎ መጀመር
2. ኢስቲአዛውን ከሱረቱ ተውባ ጋር በማያያዝ ማንበብ ናቸው።

## በስመላህ በሁለት ሱራዎች መካከል

በስመላህ ከሱረቱ ተውባ ውጭ ባለ በሁለት ሱራዎች መካከል ሶስት አይነት አነባበብ አሉት። እነሱም፡-

1. ሁሉንም ምቁረጥ
2. በሱራው የመጨረሻ አንቀፅ ላይ ማቆም ከዚያም በስመላንና የሚቀጥለውን ሱራ ማያያዝ

ሁሉንም ማያያዝ

ነገር ግን በስመላን በሁለትሱራዎች መካከል ማንበብ የማይቻልበት መንገድ የመጀመሪያውን ሱራ መጨረሻ አንቀፅ ከበስመላ ጋር አያይዞ በማቆም የሚቀጥለውን ሱራ በማንበብ ጊዜ ነው። ምክንያቱም በዚህ ጊዜ በስመላ የመጀመሪያው ሱራ የመጨረሻ አንቀፅ ስለሚሆን ነው። ነገር ግን በስመላ የማንኛውም ሱራ የመጨረሻ አንቀፅ አይደለም።

# የኑነሳኪናና የተንዊን ህጎች

ኑነሳኪና ማለት የአረበኛ ፊደል የሆነችው ኑን ሱኩን ሆና ስትመጣ ማለት ሲሆን በቁርአን ውስጥ ሱኩን በሁለት አይነት መልኩ ተፅፋ እናገኛታለን።

1. ኑን ላይ የይበልጣል የሚመስል ቅርፅ ሲመጣ(ስኩን ምልክት ሲመጣ)
2. ኑን ላይ ምንም አይነት ምልክት ሳይኖራት ሲቀር

ተንዊን ማላት በሃያ ስምንቱ /28/ የአረብኛ ፊደሎች ላይ ፈትሀተይን፣ ከስረተይን እና ዶማተይን ሲመጣ ማለት ነው። ኑነሳኪናና ተንዊን በአንድ ላይ ሊጠኑ የተፈለገበት ምክንያት ሁለቱም መጨረሻ ላይ ን የሚል ድምፅ ስላላቸው ነው።

ኑነሳኪናና ተንዊን ሀያ ስምንቱን /28/ የአረብኛ ፊደሎች በአንድነት በመያዝ አራት ህጎች አላት። እነሱም፡-

1. አልኢዝሀር
2. አልኢድጋም

3. አልኢቅላብ
4. አልኢኽፋእ ናቸው።

በተጅዊድ ህግ መሰረት ለሁሉም ህጎች ምሳሌ መስጠት የሚቻለው ከቁርአን ብቻ ነው።

## 1. አልኢዝሀር

ኢዝሀር ማለት በቋንቋ ደረጃ፡-<<ግልፅ ማድረግ ማለት ነው።>>

ኢዝሀር በተጅዊድ መሁራኖች አነጋገር፡-<<እያንዳንዱን የኢዝሀር ፊደል ጉናን ካለመጠቀም ከመውጫቸው ግልፅ አድርጐ ማውጣት ማለት ነው።>>

የኢዝሀር ፊደሎች ስድስት /6/ ናቸው። እነሱም

أ ه ع ح غ خ

## 2. አልኢድጋም

አልኢድጋም በቋንቋ አነጋገር፡-<<አንድን ነገር ወደ አንድ ነገር ውስጥ ማስገባት ማለት ነው።>>

ኢድጋም በተጅዊድ ምሁራኖች አነጋገር፡-<<ኑነሳኪናን ወይንም ተንዊንን ከተሀረከው የኢድጋም ፊደል ጋር በማያያዝ ልክ እንደ አንድ ሽዳ የሆነ ፊደል አድርጎ ማንበብ ማልት ነው።>>

የኢድጋም ፊደሎች ስድስት /6/ ሲሆኑ በአንድነት የርሙሉን

(ي ر م ل و ن) (يرملون)

ጉና ማለት በቋንቋ ደረጃ፡- <<ከኮሽኮሾ(አፍንጫ ውስጥ የሚገኝ ክፍል)የሚወጣ ድምፅ ማለት ነው።>>

በተጅዊድ ምሁራኖች አተረጓጎም ደግሞ፡- <<በኑንና በሚም አካል ላይ የሚገኝ ማራኪና ታፋጭ የሆነ ድምፅ ማለት ነው።>>

ኢድጋም ስድስቱን /6/ ፊደሎች መያዝ ለሁለት /2/ ይከፈላል።

1.ኢድጋም ቢጉናህ
2.ኢድጋም ቢገይሪጉናህ

### 1. ኢድጋም ቢጉናህ

ኢድጋም ቢጉናህ ማለት ከኑነሳኪናና ከተንዊን በኋላ የኢድጋም ቢጉናህ ፊደሎች ሲመጡ ኑነሳኪናንና ተንዊኑን ከፊደሎቹ ጋር በማያያዝና ጉናን በመጠቀም ማንበብ ማለት ነው።

የኢድጋም ቢጉናህ ፊደሎች አራት /4/ ናቸው። እነሱም የንሙ ( ي ن م و ) (ينمو) ናቸው።

## 2. ኢድጋም ቢገይሪ ጉና

የኢድጋም ቢገይሪ ጉና ፊደሎች ሁለት /2/ ሲሆኑ እነሱም ላም ( ل ) እና ራዕ ( ر ) ናቸው። ላምና ራዕ ከኑነሳኪናና ከተንዊን በኃላ ከመጣ ኑነሳኪናውን ወይም ተንዊኑን ከላም ወይም ከራዕ ጋር በማያያዝ ጉናን ሳንጠቀም እናነበዋለን።

## 3. አልኢቅላብ

ኢቅላብ በቋንቋ ደረጃ፡- <<አንድን ነገር ፊቱን ማዞር (መገልበጥ) ማለት ነው።>>

ኢቅላብ በተጅዊድ ምሁራኖች አነጋገር፡- <<ከባዕ በፊት የመጣውን ኑንሳኪናና ተንዊን ኢኽፋዕና ጉናን በመጠቀም ወደ ሚምነት በመገልበጥ ማንበብ ማለት ነው።>>

የኢቅላብ ፊደል አንድ ሲሆን እሱም ባዕ ( ب ) ነው።

፨ በቁርአን ውስጥ የኢቅላብ ምሳሌ መሆኑን የምንለይበት ዘዴ

1. በኑነሳኪና ላይ ትንሽ ሚም ሲመጣ
2. በተንዊን አንድ ፈትሀ ፣ ከስራና ዶማ ላይ ትንሽ ሚም ሲመጣ

## 4. አልኢኽፋዕ

ኢኽፋዕ በቋንቋ አነጋገር፡- <<መሸሸግ መደበቅ ማለት ነው።>>

ኢኽፋዕ በተጅዊድ ምሁራኖች አነጋገር፡- <<በመጀመሪያው ፊደል ላይ ጉና ከመኖር ጋር ፊደሉ ከመጥበቅ ያገለለና ፊደሉን በኢዝሀርና በኢድጋም መካከል በሆነ ሁኔታ መናገር ማለት ነው።>>

የኢኽፋዕ ፊደሎች አስራ አምስት ናቸው። እነሱም

( ت ث ج د ذ ز س ش ص ض ط ظ ف ق ك )

## የሚመሳኪና ህጎች

ሚመሳኪና ማለት ሚም ሱኩን ሆና ስትመጣ ማለት ነው። ሚመሳኪና ህያ

ስምንቱን/28/ የአረብኛ ፊደሎች በመያዝ ሶስት ህጎች አሏት። እነሱም፡-

1. አልኢኽፋዕዕ
2. አልኢድጋም
3. አልኢዝሀር ናቸው።

## 1. አልኢኽፋዕ

የኢኽፋዕ ፊደል ባዕ (ب) ሲሆን ከሚመሳኪና በኃላ ባዕ በሚመጣበት ጊዜ ሚመሳኪናው ኢኽፋዕ ተደርጎ ይነበባል።
ይህ የኢኽፋዕ ክፍል <<ኢኽፋዕ ሸፈውይ>> ተብሎ ይጠራል።

## 2. አልኢድጋም

የኢድጋም ፊደል ሚም (م) ሲሆን ከሚመሳኪን በኃላ ሚም በሚመጣበት ጊዜ የመጀመሪያውን ሚም ጉና በመጠቀም ኢድጋም ማድረግ ግዴታ መሆኑን ሁሉም የተጅዊድ ምሁራኖች ይስማማሉ።
ይህ የሚመሳኪና ክፍል <<ኢድጋም ሚስለይኒ ሰጊራ>> ተበሎ ይጠራል።

## 3. አልኢዝሀር

ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት/2/ ፊደሎች ውጭ ያሉት ሀያ ስድስቱ/26/ የአረበኛ ፊደሎች ከሚመሳኪና በኃላ ሲመጡ ውሳኔያቸው ኢዝሀር /ግልፅ/ አድርጎ ማንበብ መሆኑን ሁሉም የተጅዊድ ምሁራኖች ይስማማሉ።
ይህ የሚመሳኪና ክፍል <<ኢዝሀር ሸፈውይ>> ተብሎ ይጠራል።

ሚምና ዋው በመውጫ ቦታቸው አንድ ሁነው ሚምና ፋዕ ደግሞ በመውጫ ቦታቸው የተቀራረቡ በመሆናቸው ምክንያት ሚም ከእነዚህ ሁለት ፊደሎች ጋር በምትገናኝበት ጊዜ ኢኽፋዕ እንዳትደረግ የተጅዊድ ምሁራኖች ያስጠነቅቃሉ።

# ሸዳ የሆኑ ሚምና ኑን ህጎች

ኑንና ሚም የጉና ፊደል ሲሆኑ ሸዳ ሆነው በሚመጡበት ጊዜ የሁለት ሀረካ ያህል ጊዜ ጉና ማድረግ ግዴታ ነው። ሀረካ የሚባለው ደግሞ ጣትን የማጠፍ ወይም የመዘርጋት ያህል ጊዜን ይወክላል።

ጉና ማለት በቋንቋ ደረጃ፡- <<ከኮሽኮሽ የሚወጣ ድምፅ ማለት ነው።>>
በተጅዊድ ምሁራኖች አተረጓጎም ደግሞ፡- <<በኑንና በሚም አካል ላይ የሚገኝ

ማራኪና ጣፋጭ የሆነ ድምፅ ማለት ነው።>>

ጉና ለሚምና ለኑን በማንኛውም አይነት ሁኔታቸው ጊዜ የሚገኝና ሊለያቸው የማይችል መሰረታዊ የሆነ ባህሪያቸው ነው።

## ላመልአል

ላመልአል ሃያ ስምንቱን/28/ የአረበኛ ፊደሎች በመያዝ ለሁለት/2/ ትከፈላለች።

1. ቀመርያ
2. ሸምስያ

## 1. ቀመርያ

ቀመርያ አስራ አራት/14/ ፊደሎች አሉት። እነሱም

( ابغ حجك وخف عقيمه )

( أ ، ب ، غ ، ح ، ج ، ك ، و ، خ ، ف ، ع ، ق ، ي ، م ، ه )

ላመልአል ከእነዚህ አስራ አራት/14/ ፊደሎች በፊት ከመጣ ላመልአሉን ኢዝሀር በማድረግ እናነበዋለን። ይህንንም <<ቀመርያ ኢዝሀር>> እንለዋለን። ላመልአሉን ደግሞ <<ላመልቀመርያ>> ብለን እንጠራዋለን።

ላመልአል ከእነዚህ አስራ አራት/14/ ፊደሎች ጋር ኢዝሀር ግልፅ ሊሆን የቻለበት ምክንያት የላም መውጫ ቦታ ከእነዚህ ፊደሎች መውጫ ቦታ በመራቁ ምክንያት ነው።

### በቁርአን ውስጥ የቀመርያን ምሳሌ የምንለይበት ዘዴ

1. ከላመልአል ቀጥሎ የሚመጣው ፊደል ላይ ሀረካ ብቻ ሲኖረው
2. ላመልአልን በምናነብበት ጊዜ ላሚ ግልጽ ስትሆን

## 2. ሸምስይ

ከላመልአል ቀጥሎ ቀሪዎቹ አስራ አራት ፊደሎች በሚመጡበት ጊዜ ላመልአሉን ከፊደሎቹ ጋር በማያያዝ እናነበዋለን።

ሸምስያ አስራ አርት/14/ ፊደሎች አሉት። እነሱም

( ط ، ث ، ص ، ر ، ت ، ض ، ذ ، ن ، د ، س ، ظ ، ز ، ش ، ل )

ላመልአል ከእነዚህ አስራ አራት /14/ ፊደሎች በፊት ከመጣ ላመልአሉን ኢድጋም በማድረግ እናነበዋልን። ይህንንም <<ሸምስያ ኢድጋም>> እንለዋለን። ላመልአሉን ደግሞ <<ላመሸምስያ>> ብለን እንጠራዋለን።

ላመልአል ከእነዚህ አስራ አራት /14/ ፊደሎች ጋር ኢድጋም ሊደረግ የቻለበት ምክንያት ላመል አል ከላም ( ل ) ጋር ተመሳሳይ ስለሆነና ከላም ውጭ ካሉ ፊደላቶች ጋር ደግሞ በመውጫ ቦታም ሆነ በባህሪ በመቀራረባቸው ምክንያት ነው።

## የሸምስያን ምሳሌ ከቁርአን ውስጥ የምንለይበት ዘዴ

1. ከላመልአል ቀጥሎ የሚመጣው ፊደል የሀረካና የሸዳ ምልክት ሲኖረው
2. ሱኩን የሆነው ላም ከተሀረከው የሸምስያ ፊደል ጋር ተያይዞ ሲነበብ

## የፊደላት መውጫ

መኽረጅ ማለት በቋንቋ ደረጃ፡- <<የማንኛውም ነገር መውጫ ቦታ ስም ነው።>>

በተጅዊድ ምሁራኖች አተረጓጎም ደግሞ፡- <<ማንኛውም ፊደል የሚወጣበት፣ ግልፅ የሚሆንበትና ከሌላው ፊደል የሚለይበት የሆነ ቦታ ነው።>>

የተጅዊድ ምሁራኖች በፊደላት መውጫ ቦታ ቁጥር ላይ ለአራት/4/ ተከፍለዋል። ተመራጭ የሆነው መንገድና በብዛት የሚሰራበት የአብዛሀኞቹ የነህው ምሁራኖችና የኢማሙ ኢብን ጀዘሪ አባባል ነው። ይህም የፊደላት መውጫ ቦት አስራ ሰባት/17/ ናቸው የሚለው ነው። አሰራ ሰባቱን የፊደላት መውጫ ቦታ ለአምስት/5/ ይከፍሉታል።

1. አልጀውፍ
2. አልሀልቅ
3. አልሊሳን
5. አልኸይሹም
4. አሸሸፈተይን

ከመድና ከሊን ፊደሎች ውጭ ያሉትን የማንኛውንም ፊደል መውጫ ቦታ ለማወቅ ፊደሉን ሱኩን ወይም ሸዳ በማድረግ ከፊደሉ በፊት በማንኛውም አይነት ሀረካ የተሀረከ ሀምዘተል ወስል ጨምሮ በማንበብ ድምፅን ማድመጥ ድምፁ የሚያቋርጥበት ቦታ የፊደሉ መውጫ ቦታ ነው።

እንዲሁም የመድና የሊን ፊደላትን መውጫ ቦታ ለማወቅ ከተፈለገ በአሊፍ ላይ ፈተሀ የሆነ ፊደል፣ በያዕ ላይ ከስራ የሆነ ፊደልና በዋው ላይ ደግሞ ዶማ የሆነ ፊደል አስገብቶ በማንበብ ድምፅን ምድመጥ ከዚያም ድምፁ የሚያቋርጥበት ቦታ ላይ የፊደሉ መውጫ ቦታ ነው።

## 1. አልጀውፍ

ጀውፍ ማለት በቋንቋ ደርጃ፡- <<ባዶ ቦታ ማለት ነው።>>

በተጅዊድ ምሁራኖች አተረጓጎም፡- <<የአፍና የጉሮሮ ባዶው ቦታ ማለት ነው።>>

ከዚህም ቦታ ሦስቱ/3/ የመድ ፊደሎች ይወጣሉ። እነሱም፡-

1. ከፊቷ ፈትሀ የመጣባት አሊፍ
2. ከፊቷ ዶማ የመጣባት ዋው
3. ከፊቷ ከስራ የመጣባት ያዕ ናቸው።

እነዚህ ሦስት ፊደሎች <<ሁሩፉል ጀውፍያህ>> ወይም <<ሁሩፉል ሀዋኢያህ>> በመባል ይጠራሉ።

እነዚህ ፊደሎች የሚወጡት ከጀውፍ ነው ሲባል አሊፍ የምትመጣው ከጉሮሮ ባዶ ቦት ላይ፣ ያዕ ከምላስ መካከለኛ ክፍል ባዶ ቦታ ላይ እንዲሁም ዋው ደግሞ ከከንፈሮች ባዶ ቦታ ላይ ይወጣሉ ማለት ነው።

## 2. አልሀልቅ

ሀልቅ አጠቃላይ የሆነ መውጫ ቦታ ሲሆን በእሱም ውስጥ ሶስት ክፍሎች አሉ።

1. አቅሰል ሀልቅ (የጉሮሮ ሩቅ ክፍል)
2. ወሰጠል ሀልቅ   (የጉሮሮ ቅርብ ክፍል)
3. አድነል ሀልቅ   (የጉሮሮ ቅርብ ክፍል)

1. አቅሶል ሀልቅ ከልብ ቀጥሎ ለአፍ ሩቅ የሆነው ክፍል ሲሆን ከዚህም ቦታ ሀምዝ( أ ) እና ሐዕ ( ه ) ይወጣሉ።

2. ወሰጠል ሀልቅ የጉሮሮ መካከለኛ ክፍል ሲሆን አይን ( ع ) እና ሃዕ ( ح ) ይወጣሉ።

2. አድነል ሀልቅ ለአፍ ቅርብ የሆነ የጉሮሮ ክፍል ሲሆን ከዚህም ገይን ( غ ) እና ኻዕ( خ ) ይወጣሉ።

እነዚህ ስድስት ፊደሎች የሚወጡት ከሀልቅ ስለሆነ <<ሀልቅያህ>> በመባል ይጠራሉ።

## 3. አልሊሳን

ሊሳን አጠቃላይ የሆነ መውጫ ሲሆን በውስጡ አስር/10/ መውጫ ክፍሎች አሉት። በእነዚህ ውስጥ አስራ ስምንት/18/ ፊደሎች ይወጣሉ። እንዚህ ፊደሎች አቅሶሊሳን፣ ወሰጠሊሳን፣ ሀፈቱሊሳንና ጦረፈሊሳን በሚባሉ የምላስ ክፍሎች ውስጥ ይጠቃለላሉ።

### አቅሶሊሳን

አቅሶሊሳን ለጉሮሮ ቅርብ ከመሆኑ ጋር ለአፍ ሩቅ የሆነው ክፍል ነው። በውስጡ ሁለት/2/ መውጫ ቦታዎች አሉት።

1. ( ق )(የቃፍ መውጫ)

ቃፍ ከጉሮሮ ቀጥሎ ከሚገኘው ከምላስ ሩቅ ክፍልና በትክክሉ ከሚገኘው ከላይኛው ላንቃ ጋር ትወጣለች።

2. ( ك )(የካፍ መውጫ)

ካፍ ከጉሮሮ ቀጥሎ ከሚገኘው ከምላስ ሩቅ ክፍልና በትክክሉ ከሚገኘው ከላይኛው ላንቃ ጋር ከቃፍ መውጫ ትንሽ ዝቅ ብሎ ይወጣል።

### ወሰጦሊሳን

ከምላስ መካከለኛ ክፍልና በትክክሉ ከሚገኘው ከላይኛው የላንቃ ክፍል ጋር

ሶስት ፊደሎች ይወጣሉ። እነሱም ( ج، ش ، ي ) ናቸው።
እዚህ ላይ የተፈለገችው ያዕ ከመድ ፊደል ውጭ የሆነችው የተሀረከች ያዕ ናት።

## ሀፊቱ ሊሳን

በዚህ የምላስ ክፍል ላይ ሁለት መውጫ ቦታዎች ይገኛል።እነሱም የዷድ( ض ) እና የላም ( ل ) መውጫ ናቸው።

## የዷድ መውጫ

ከምላስ ከአንደኛው ጎን በኩልና ማለትም ከያዕ መውጫ በኋላ፣ ከላም መውጫ በፊት ከላይኛው መንጋጋ ጥርስ ቀጥሎ ከሚገኘው የምላስ ክፍል ዷድ ( ض ) ትወጣለች።

ዷድን ( ض ) ከግራ በኩል ማውጣት ቀላልና ብዙዎቹ ቃሪኦች የሚጠቀሙበት ነው። ከቀኝ በኩል ማውጣት ደግሞ አስቸጋሪና ጥቂት ሰዎች የሚጠቀሙበት ሲሆን በሁለቱም ጎኖች ማውጣት ደግሞ በጣም አስቸጋሪና ከባድ ነው።

ነብዩ ሙሃመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ዷድን የሚያወጡት በሁለቱም ጎን ነበር። እንደዚሁም ኡመር ኢብን ኸጧብ (ረ.ዐ) ልክ እንደነብዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ አስመስሎ ዷድን የሚያወጣው በሁለቱም ጎኖች ነበር።

በጥቅሉ የዷድ መውጫ አስቸጋሪና በምላስ ላይ ብርቱ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ ሰዎች ዷድን በሚያወጡበት ጊዜ ስህተት ይፈፅማሉ። በመሆኑም የዷድ መውጫ የሚታወቀው ከብዙ ልምምድና ትግል (ጥረት) በኃላ ብቻ ነው።

## የላም መውጫ

ከዷድ መውጫ በኃላ ከአንደኛው የምላስ ጎንና በትክክሉ ከሚገኘው ከላይኛው ጥርስ መባቀያ ጋር ላም ( ل ) ትወጣለች። ላም ልክ እንደ ዷድ በሁለቱም ጎን መውጣት ትችላለች። ነገር ግን በዷድ ተቃራኒ ላምን ከቀኝ በኩል ማውጣት ቀላልና ብዙዎቹ የተጅዊድ ምሁራኖችና ቃሪኦች የሚጠቀሙበት ነው።

## ጦረፉሊሳን

በምላስ ጫፍ ላይ አምስት/5/ መውጫ ቦታዎች አሉ።

### 1. የኑን መውጫ

በማንኛውም አይነት ሀረካ የተሀረከችና ሱኩን ሆና ኢዝሀር የምትደረግ ኑን( ن ) ትንሽ ከላም መውጫ ቦታ ዝቅ ብላ ከምላስ ጫፍና በትክክሉ ከሚገኘው ከላይኛው ጥርስ መባቀያ ላይ ትወጣለች።

ኢዝሀር የምትደረግ ኑን ብሎ መለየት ያስፈለገው ኢድጋምና ኢኽፋዕ ከሚደረገው ኑን ለመለየት ተፈልጎ ነው። ምክንያቱም ኢኽፋዕና ኢድጋም የሚደረገው ኑን መውጫ ቦታ ኮሽኮሽ ላይ ስለሆነ ነው።

### 2. የራዕ መውጫ

ከምላስ ጫፍ ከኑን መውጫ በኃላ ትንሽ ወደ ምላስ ጀርባ ያዘነበለ ሆኖ በትክክሉ ከሚገኘው ከላይኛው ጥርስ መባቀያ ጋር ራዕ ( ر ) ትወጣለች።

### 3. የጧዕ፣ የዳልና የታዕ መውጫ

የምልስጫፍ ጀርባ ከላይኛው ሁለት የፊት ጥርሶች መባቀያ ጋር ጧዕ፣ ዳልና ታዕ ይወጣሉ።

### 4. የሷድ፣ የሲን እና የዛይ መውጫ

የምላስ ጫፍ ከላይኛው የፊት ጥርስ ጫፍና ከታችኛው የፊት ጥርስ ጫፍ መካከል ከሚገኘው ትንሽ ወደ ታችኛው የፊት ጥርስ ጫፍ የቀረበ ሲሆን ሷድ፣ ሲንና ዛይ ይወጣሉ።

### 5. የዟዕ፣ የዛል እና የሳዕ መውጫ

የምላስ ጫፍ ከላይኛው የፊት ጥርስ ጫፍ ጋር ዟዕ፣ ዛልና ሳዕ ይወጣሉ።

## 4. አሸሸፈታን

በሁለት ከንፈሮች መካከል ሁለት/2/ መውጫ ቦታዎች አሉ።

1. የፋዕ መውጫ ቦታ

የታችኛው ከንፈር የውስጠኛው ክፍል ከላይኛው ሁለት የፊት ጥርሶች ጫፍ ጋር ፋዕ ትወጣለች።

2. የዋው፣ የሚም እና የባዕ መውጫ ቦታ

እነዚህ ሶስት/3/ ፊደሎች በሁለት ከንፈሮች መካከል ይወጣሉ። ነገር ግን ዋው በሚወጣበት ጊዜ ሁለቱ ከንፈሮች ትንሽ ሲከፈቱና ሲለያዩ ባዕና ሚም በሚወጡበት ጊዜ ደግሞ ሁለቱም ከንፈሮች ከሚጋጠሙት ይልቅ ባዕ በምትወጣበት ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ይጋጠማሉ።

## 5. አልኸይሹም

ኮሽኮሽ ማለት የአፍንጫ ሩቅ ክፍል /ከውስጠኛው የአፍ ክፍል ጋር/ የሚያገናኘው የአፍንጫ ቀዳዳው ክፍል ማለት ነው። ኮሽኮሽ ውስጥ አንድ መውጫ ቦታ አለ። ከዚህም ቦታ ጉና ይወጣል።

የተጅዊድ ምሁራኖች ኑንና ሚም ሸዳ ሆነው በሚመጡበት ጊዜ በፊደሎቹ የመናገር ጊዜ ጉናን ኢዝሀር /ግልፅ/ ማድረግ ግዴታ ነው ይላሉ።

ኮሽኮሽ ለፊደሎች /ኑንና ሚም/ መውጫ ቦታ ሳይሆን የፊደሎቹ ባህሪ ለሆነው ጉና መውጫ ቦታ ነው።

እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፍ ነገር ቢኖር የአረብኛ ፊደላት ቁጥር በፊደላት መውጫና በፊደላት ባህሪ ጊዜ ሰላሳ አንድ/31/ ፊደሎች ናቸው። ማለትም፡-

በጀውፍ ሦስት/3/ ፊደሎች፣ በሁልቅ ስድስት/6/ ፊደሎች፣ በምላስ የተለያዩ ክፍሎች አስራ ስምንት/18/ ፊደሎችና በሁለቱ ከንፈሮች አራት/4/ ፊደሎች ናቸው።

በኑነሳኪናና ተንዊን፣ በሚመሳኪናና ሱኩን በሆኑ ላሞች ህግ ጊዜ የአረበኛ ፊደሎች ቁጥር ሃያ ስምንት/28/ ፊደሎች ይሆናሉ። ይህም የሆነበት ምክንያት ሶስቱ የመድ ፊደሎች ከኑነሳኪናና ተንዊን በኃላ መምጣት ስለማይችሉ ነው።

## በማንኛውም ሁኔታ የሚወፍሩ ፊደሎች

በማንኛውም ሁኔታ የሚወፍሩ ፊደሎች ሰባቱ የኢስቲዕላ ፊደሎች ናቸው።
ኢስቲዕላዕ ማለት ቋንቋ ደረጃ፡- << ከፍታ ማለት ነው።>>

በተጅዊድ ምሁራኖች አተረጓጎም ደግሞ፡- <<የኢስቲዕላዕን ፍደል በመናገር ጊዜ ምላስ ወደ ላይኛው ላንቃ ክፍል ከፍ ማለት ኢስቲዕላዕ ይባላል።>>
የኢስቲዕላዕ ፊደሎች ሰባት ናቸው። እነሱም

( خ ، ص ، ض ، ط ، ظ ، غ ، ق )

ሰባቱ የኢስቲዕላዕ ፊደሎች የብርታት ደረጃ እንደሚከተለው ነው።

1. الطاء 2. الضاد 3. الصاد 4. الظاء 5. القاف 6. الغين 7. الخاء

## ቀልቀላህ

ቀልቀላህ ማለት በቋንቋ ደረጃ፡- <<መንቀሳቀስ አለመረጋጋት ማለት ነው።>>

በተጅዊድ ምሁራኖች አተረጓጎም ደግሞ፡- <<ፊደሉ ሙሉ የሆነ ግልጽ መሆንን ግልጽ እንዲሆን ሱኩን የሆነው ፊደል በመውጫው ቦታ ላይ ያለው ድምጽ ያለምረጋጋት ሃይል ማለት ነው።>>

የቀልቀላ ፊደሎች አምስት ናቸው። እነሱም፡- (قطب جد)

( ق ، ط ، ب ، ج ، د )

የቀልቀላ ፊደሎች የቀልቀላነት ደረጃዎች ሦስት ናቸው።

1. በከፍተኛ ደረጃ ቀልቀላ የሚደርግ

   ፊደሉ ሸዳ ሆኖ እዚያው ፊደል ላይ የሚቆም ሲሆን

2. በመካከለኛ ደረጃ ቀልቀላ የሚደረግ

ፊደሉ ሸዳ ሳይኖረው እዚያው ፊደል ላይ የሚቆም ሲሆን

3. በዝቅተኛ ደረጃ ቀልቀላ የሚደረግ

ፊደሉ ሱኩን ሆኖ እዚያው ፊደል ላይ የማይቆም ሲሆን።

## አልመድ

መድ ማለት በቋንቋ ደረጃ፡- <<ጭማሬ ማለት ነው።>>

በተጅዊድ ምሁራኖች አተረጓጎም ደግሞ፡- <<የመድ ወይም የሊን ፊደሎችን እንዲረዝሙ የሚያደርጉ ምክንያቶች የመገኘት ጊዜ የፊደሎቹ ድምፅ መርዘም ማለት ነው።>>

የመድ ፊደሎች ሶስት /3/ ሲሆኑ እነሱም

1. ከፊቷ ፈትሀ የሚመጣባት አሊፍ
2. ከፊቷ ከስራ የሚመጣባት ያዕና
3. ከፊቷ ዶማ የሚመጣባት ዋው ናቸው።

ሁሉም የመድ ፊደሎች በአንድ ላይ ( نُوحِيهَا ) በሚለው የቁርአን አንቀፅ ላይ ተሰብስበው እናገኛቸዋለን። ዋውና ያዕ ሱኩን ሆነው ከፊታቸው ፈትሀ ከመጣ የሊን ፊደል ይሆናሉ።

እነዚህ ሶስት የመድ ፊደሎች የመድ ፊደል ተብለው ሊጠሩ የቻሉበት ምክንያት በነሱ ድምፅ የሚራዘም በመሆኑ ሲሆን የሊን ፊደሎች የሊን ፊደል ተብለው ሊጠሩ የቻሉበት ምክንያት ደግሞ በገርነትና ምላስን ያለማስቸገር የሚወጡ በመሆናቸው ነው።

የተጅዊድ ምሁራኖች መድን አስልይ እን ፈርዕይ በማለት ለሁለት ይከፍሉታል።

## 1. መደል አስልይ

ከፊቱ ሀምዝ ከኋላው ደግሞ ሀምዝና ሱኩን ያልመጣበት የሆነ የመድና የሊን ፊደል መደል አስልይ ይባላል።

መደል አስልይ ማለት መደ ጦብዕይ ማለት ነው። መደል አስልይ የሁለት ሀረካ ጊዜ ያህል ይሳባል። ሁለት ሀረካ ማለት ደግሞ በመካከለኛ ሁኔታ እጅን ማጠፍ ወይም መዘርጋት ማለት ነው።

## 2. መደል ፈርዕይ

መደል ፈርዕይ ማለት ከዚህ በታች በሚመጡ ሁኔታዎች ምክንያት ከመደ ጦብዕይ በላይ የሆነ የመድ ጭማሬ ማለት ነው።

የመደል ፈርዕይ አይነቶች ሁለት ሲሆን እነሱም ሀምዝን ሱኩን ናቸው።

የመደል ፈርዕይ አይነቶች አምስት ናቸው። እነሱም፡-

1. መደል በደል
2. መደል ሙተሲል
3. መደል ሙንፈሲል
4. መደል አሪዺን ሊሱኩን
5. መደላዚም ናቸው።

**ሀምዝ ለመደል በደል፣ ለመደል ሙተሲልና ለመደል ሙንፈሲል ምክንያት ሲሆን ሱኩን ደግሞ ለመደል ላዚምና ለመደል አሪዺን ሊሱኩን ምክንያት ነው።**

## 1. መደል በደል

መደል በደል ማለት ከመድ ፊደል በፊት ሀምዝ ሲመጣ ማለት ነው። ከመደል በደል በኋላ ሀምዝም ሆነ ሱኩን አይመጣም።

መደል በደል ውሳኔው በሀፍስ ቂርአት አይነት የሁለት ሀረካ ያህል ይሳባል።

## 2. መደል ሙተሲል

መደል ሙተሲል ማለት በአንድ ቃል ላይ ከመድ ፊደል በኋላ ሀምዝ ሲመጣ ማለት ነው።

የመደል ሙተሲል ውሳኔ በሀፍስ የቂርአት አይነት ተቀጥሎ በሚነበብበት ጊዜ አራት ወይም አምስት ሀረካ የሚሳብ ሲሆን በሚቆምበት ጊዜ ግን ስድስት ሀረካ ይሳባል።

ይህ የመድ ክፍል መደል ሙተሲል የተባለበት ምክንያት ሀምዙና የመዱ ፊደል በአንድ ቃል ላይ የተያያዙ ስለሆኑ ነው።

## 3. መደል ሙንፈሲል

መደል ሙንፈሲል ማለት በሁለት ቃላት ላይ በመጀመሪያው ቃል መጨረሻ ላይ የመድ ፊደል መጥቶ በሁለተኛው ቃል መጀመሪያ ላይ ሀምዝ ሲመጣ ማለት ነው።

የመደል ሙንፈሲል ውሳኔው ሁለት ሀረካና ከዚያ በላይ መሳብ ይቻላል። ነገር ግን

በሀፍስ የቂርአት አይነት አራት ወይም አምስት ሀረካ ይሳባል።

## 4. መዱል አሪዲን ሊሱኩን

መዱል አሪዲን ሊሱኩን ማለት ከመድ ወይም /ከሊን ፊደል/ በኋላ የማቆም ጊዜ ድንገተኛ የሆነ ሱኩን መምጣት ማለት ነው ።

የመዱል አሪዲን ሊሱኩን ውሳኔው የቀስር፣ የተወሱጥም ሆነ የመድ ሀርካ ያህል ጊዜ መሳብ ይቻላል። ቀስር ማለት በመዱ ላይ የሁለት ሀረካ ጊዜ ያህል መዘግየት ማለት ነው። ተወሱጥ ማለት በመዱ ላይ የአራት ሀረካ ጊዜ ያህል መዘግየት ማለት ነው። መድ ማለት ደግሞ በመዱ ላይ የአምስት ሀረካ ጊዜ ያህል መዘግየት ማለት ነው።

## 5. መደልላዚም

መደልላዚም ማለት በቃል ወይም በፊደል ላይ ከመድ ከሊን ፊደል በኃላ በምናቆምበትም ሆነ በምንቀጥልበት ጊዜ መሰረታዊ የሆነ ሱኩን መምጣት ማለት ነው።

ይህ የመድ አይነት መደላዚም ተብሎ ሊጠራ የቻለበት ምክንያት መዱ ምንግዜም ስድስት ሀረካ ያህል የሚሳብ ስለሆነና ለመዱ መሳብ ምክንያት የሆነው ሱኩን በምናቆምበት ሆነ በምንቀጥልበትም ጊዜ የሚገኝ በመሆኑ ነው።

መደልላዚም ለአራት /4/ ይከፈላል።

1. መደላዚም ከሊሚዩን ሙሰቀል
2. መደላዚም ከሊሚዩን ሙኸፈፍ
3. መደላዚም ሀርፊዩን ሙሰቀል
4. መደላዚም ሀርፊዩን ሙኸፈፍ ናቸው።

### 1. መደላዚም ከሊሚዩን ሙሰቀል

በአንድ ቃል ላይ ከመድ ፊደል በኋላ ሽዳ የሆነ ፊደል በሚመጣበት ጊዜ መደልላዚም ሙሰቀሉስ ከሊሚይ ይባላል። መዱንም ስድስት ሀረካ ስበን እናነባለን።

### 2. መደላዚም ከሊሚዩን ሙኸፈፍ

በአንድ ቃል ላይ ከመድ ፊደል በኋላ ሱኩን የሆነ ፊደል በሚመጣበት ጊዜ መደልላዚም ሙኸፈፉል ከሊሚይ ይባላል። መዱንም ስድስት ሀረካ ስበን እናነባለን።

## 3. መደላዚም ሀርፊዩን ሙሰቀል

በአንድ ፊደል ላይ ከመድ ፊደል በኋላ መሰረታዊ የሆነ ሱኩን መምጣትና ሱኩኑን ከሚቀጥለው ፊደል ጋር ኢድጋም አድርጎ ማንበብ ማለት ነው።

የዚህ መድ መገኛ ቦታዎች በሱራዎች መጀመሪይ ላይ ነው። መዱ ያለበት ፊደል ተበትኖ ሲጻፍ ከሶስት ፊደሎች የተመሰረተ ነው። መካከለኛው ፊደል የመድ ፊደል ሲሆን ሶስተኛው ፊደል ደግሞ ከሚቀጥለው ፊደል ጋር ኢድጋም የሚደረግ ነው።

## 4. መደላዚም ሀርፊዩን ሙኸፈፍ

በአንድ ፊደል ላይ ከመድ ፊደል በኋላ መሰረታዊ የሆነ ሱኩን መምጣትና ሱኩን የሆነውን ፊደል ከሚቀጥለው ፊደል ጋር ኢድጋምን ካለመጠቀም /ግልፅ በማደርግ/ ማንበብ ማለት ነው።

ከላይ በሶስተኛው የመድ ክፍል እንዳሳለፍነው የመዱ መገኛ ቦታውች በሱራዎች መጀመሪያ ላይ ነው። መዱ ያለበት ፊደል ተነጣጥሎ ሲፃፍ ከሶስት ፊደሎች የተመሰረተ ነው። መካከለኛው ፊደል የመድ ፊደል ሲሆን ሶስተኛው ፊደል ደግሞ ሱኩንና ኢድጋምን ካለመጠቀም ግልፅ ተደርጎ የሚነበብ ነው።

መደል ላዚም ሀርፊይ በሁለቱም ክፍሎቹ በቁርአን ውስጥ የመዱ መገኛ ቦታዎች በሱራዎች መጀመሪያ ላይ ነው። ፊደሎቹም ስምንት ናቸው። እነሱም ( سنقص علمك ) ማለትም ( س ، ن ، ق ، ص ، ع ، ل ، م ، ك )

ከእነዚህ ስምንት ፊደሎች ውጭ የሆኑ ፊደሎች በሱራዎች መጀመሪያ ላይ በሚመጡበት ጊዜ የመደጦብዕይ የሁለት ሀረካ ጊዜ ያህል ይሳባል። ይህም የሚሆነው በአምስት ፊደሎች ላይ ነው።

እነሱም፡- ( حي طهر ) ማለትም ( ح ، ي ، ط ، ه ، ر ) ናቸው።